የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ቀን ፪ሺ.፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 16
ADDIS ABABA 20th February, 2020

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፬፻፷፬/፪ሺ.፲፪ ዓ.ም
የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ................ገጽ ፲፪ሺ.፩፻፵፰

**Content**

Regulation No. 464/2020
Defense Engineering Industry Corporation establishment Council of Ministries Regulation …………...Page 12148

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፷፬/፪ሺ.፲፪

**Council of Ministers Regulation No. 464/2020**

## የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንደስትሪ ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፺፯/፪ሺ.፲፩ አንቀጽ ፭ እና ፴፬ እንዲሁም በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ (፩) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## Defense Engineering Industry Corporation Establishment Council of Ministers Regulation

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.1097/2018 and Article 47(1) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፷፬/፪ሺ.፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1. Short Title

This Regulation can be cited as “Defense Engineering Industry Corporation establishment Council of Ministries Regulation No.464/2020 .”

### ፪. መቋቋም

፩/ የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኮርፖሬሽኑ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

### 2. Establishment

1/ The Defense Engineering Industrial Corporation (hereinafter the “Corporation”) is hereby established as an autonomous Federal Government Organ having its own legal personality.

2/ The Corporation shall be governed by the public Enterprises proclamation No. 25/1992.

### ፫. ተቆጣጣሪ ባለስልጣን

የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የመከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

### 3. Supervising Authority

The Ministry of Defense shall be the supervising Authority of the corporation.

፬. **ዋና መስሪያ ቤት**

የኮርፖሬሽኑ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ስፍራዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. **ዓላማ**

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው:-

፩/ የሀገሪቱን የመከላከያ አቅም ለማሳደግ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ዲዛይን ማድረግ፣ ማምረት፣ መትከልና ኮሚሽን በማድረግ ለምርት ማዘጋጀት፤

፪/ ለመከላከያና ለጸጥታ ሀይሎች የሚያገለግሉ የጦር መሳሪያዎችን፣ ቀላልና ከባድ ተሽከርካሪዎችንና ታንኮችን፣ የውጊያ ትራንስፖርት አውሮፕላኖችንና ሄሊኮፕተሮችን ተተኳሾችን፣ መለዋወጫዎቻቸውንና አባሪ እቃዎችን፣ ወቅቱንና የወደፊት ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ ዲዛይን በማድረግ፣ በማምረት፣ በመጠገን፣ በማደስ፣ በማሻሻል እንዲሁም በዘርፉ የማማከርና የማሰልጠን አገልግሎትን መስጠት ሽያጫቸውንም በአገር ውስጥና በውጭ ሀገር ማከናወን፤

፫/ ለመከላከያና ለጸጥታ ሀይሎች ከሚሰጡ አገልግሎቶችና ምርቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ለሲቪል አገልግሎት የሚውሉ የካፒታል እቃዎችን፣ ኬሚካሎችን እና ደማሚቶችን፣ ለወታደራዊና ለሲቪል አገልግሎቶች የሚውሉ የአቪዬሽን ምርቶችን፣ የኤሌክትሮኒክስ፣ የኦፕትሮኒክስና የኤሌክትሮ መካኒካል ምርቶችን፣ ኢንዱስትሪያል ማሽኖችን፣ መለዋወጫዎቻቸውንና አባሪ እቃዎችን ማምረት፣ መገጣጠም፣ መጠገን፣ ማደስ፣ ማሻሻል እና ተያያዥ አገልግሎቶቻቸውን መስጠትና፣ ሽያጫቸውንም በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ማከናወን፤

፬/ ከሀገሪቱ የመከላከያ ሃይል ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ አንጻር በመንግስት ውሳኔና በጀት ሊሰሩ የሚችሉ ወቅታዊና ለሀገር ደህንነት ጠቀሜታ ያላቸውን የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን፤

፭ በኮርፖሬሽኑ የሚመረቱ ምርቶችን ከአገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ ኤክስፖርት ማድረግ ፤

፮ አቅም ካላቸው የውጭ አገራት ኩባንያዎች ጋር በሽርክና በመስራት ጥራት ያላቸውን ምርቶች ማምረት፤

4. **Head Office**

The Corporation shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere in other parts of the country as may be necessary.

5. **Objectives**

The corporation shall have the objectives to:

1/ Design manufacturing industries and manufacture products, plant and undertake Commissioning so as to make ready them for production to enhance the defense capacity of the country;

2/ design with updated and proactive needs of items, to manufacture, repair maintain, modify and also conduct consultations and training services in the artilleries, small and heavy vehicles, tanks , military and transport airplanes and helicopters, firearms With respective spare part and accessories for sale domestically and abroad;

3/ Undertake manufacturing, assembling, repair, maintenance, modification and purpose incidental services, thereby conducting local and foreign patronages of defense and security services and goods along with capital items, chemicals and explosives intended for relevant civil services and also aviation products intended for military and civil purpose, as well as electronics, Optronics and electromechanical products, industrials machinery, their spare parts and respective accessories for sale domestically and abroads;

4/ engage in current technological capacity building work that is valuable for national safety being affordable and compliant to the budget of the state in consideration of the strategic interest of the National Defense force;

5/ Export products manufactured by the corporation;

6/ Establish Joint venture with other international companies;

፯ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ስራዎችን መስራት፡፡

## ፮. <u>ካፒታል</u>

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው የካፒታል መጠን ብር ፰ **ቢሊዮን** (ስምንት ቢሊየን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፪ ቢሊዮን ፫፻፵፫ ሚሊዮን ፬፻፺፪ ሺ ፱፻ ከ፶፬ ሣንቲም (ሁለት ቢሊየን ሶስት መቶ አርባ ሶስት ሚሊየን አራት መቶ ዘጠና ሁለት ሺ ዘጠኝ መቶ ብር ከሃምሳ አራት ሳንቲም) በጥሬ ገንዘብ እና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

## ፯. <u>ኃላፊነት</u>

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በእዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## ፰. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ፤</u>

በደንብ ቁጥር ፩፻፹፮/፪ሺ፪ በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ስር የነበሩት ጋፋት አርማመንት፣ ሆሚቾ አሙኒሽን ኢንጂነሪንግ፣ ደጀን አቪየሽን ኢንጂነሪንግ እና የፊውል/ነዳጅ እና ፕሮፒላንት መብትና ግዴታቸው በዚህ ደንብ ወደ ኮርፖሬሽኑ ተዛውሯል፡፡

## ፱. <u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

## ፲. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**



7/ engage in, any other related activities necessary to attain its objectives.

## 6. <u>Capital</u>

The authorized capital of the Corporation shall be Birr 8,000,000,000.00 (Eight billion Birr) of which Birr 2,343,492,900.54 (Two billion three hundred forty three million four hundred ninety two thousand nine hundred and fifty four cents) is paid up in cash and in kind.

## 7. <u>Liability</u>

The corporation shall not be liable beyond its assets.

## 8.<u>Transferring of Obligations and right</u>

The rights and obligations of Gafat armament Engineering industry, Homicho Ammunition Engineering industry, Dejen Aviation Engineering industry and fuel and propellant sub industry under the regulation number 186/2010 are hereby transferred to the Corporation under this regulation:

## 9. <u>Duration of the corporation</u>

The corporation shall remain in effect for indefinite period of time.

## 10. <u>Effective Date</u>

This regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Addis Ababa this 20th day of February 2020**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**